በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 1-31 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እና ከሰፕቴምበር 1-30/2024 የሚኖረው ወርሃዊ የአየር ጠባይ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ - 1 -

ምስል 1፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ72 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1-31/2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር - 7 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈው የኦገስት የመጀመሪያው እና ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በኦገሰት የሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ተጠናክረው የተስተዋሉ ሲሆንና በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው፡፡


በአጠቃላይ በኦገስት ወር የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ተደጋጋሚነት ያለው ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በባህርዳር 53.4፣ በነቀምት 52.3፤ በአይደርመቆ 61፣ በአልጌ 70፣ 50፤ በአማን 56.9፤ በአምደወርቅ 52.0፤ በአንግርጉትን 53.6፤ በአሶሳ 56.6፣ 57፤ በአጽቢ 52.5፣ 64፣ 74፤ በአየዉ 50፣ 57፤ በቡለን 51.4፣ 54.4፣ 84.6፤ በጨፋ 75.6፤ በዳሊፋጊ 54.2፤ በዶሎመና 50.3፤ በኢጃጂ 66.2፤ በፍቼ 80.8፤ በፉኙዶ 68፤ በገለምሶ 95.0፤ በወሊሶ 59፤ በጉንዶ መስቀል 57.2፤ በሃረር 80.3፤ በጃራ 51.4፤ በላይብር 76፤ በማጀቴ 79.4፣ 53.8፤ በመተማ 52፣ 73.6፣ 50.7፤ በሞጣ 61.1፤ በነጆ 63.4፤ በኑሬ ኤራ 67.8፤ በሻዉራ 62.6፤ በሸርቆሌ 59፤ በሽሬ 53.7፤ በስሪንቃ 55.1፤ በቴፒ 84.8፤ በጨለንቆ 63.0፤ በኩርፋ ጨሌ 77.4፤ በቁሉቢ 52.6፤ በጉብሪዬ 54.1 እንዲሁም በግራዋ 60.0 ሚ.ሜ. የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፈው የኦገስት ወር በ106 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ስፈራዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 60-95 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከበድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በገለምሶ፤ በቴፒ፤



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በቡለን፣ በፍቼ፣ በሃረር፣ በማጂቴ፣ በኩራፋ ጨሌ፣ በላይብር፣ በጨፋ፣ በአፅቢ፣ በመተማ፣ በአልጌ፣ በፉጉዶ፣ በኑራ ኤራ፣ በኢጃጂ፣ በነጆ፣ በጨለንቆ፣ በሻዉራ፣ በሻምቡ፣ በሞታ፣ በአይደርመቆ፣ በግራዋ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል 1፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ72 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የማዕከላዊ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋግህምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ አርሲ ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ ጋቢ እና አውሲ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን እና ኤረር ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ ዞን ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና አማሮ ዞኖች ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዠንግ ዞኖች እንድሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የነሀሴ ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግብርናው የስራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተለይም በማደግ፣ በማበብና ፍሬ በመሙላትም ላይ ባሉ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦት በተሻለ ሁኔታ እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር፡፡

በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ ክስተቶች፣ የመሬት አቀማመጣቸው ከፍተኛና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት፣ መሰንጠቅና ናዳ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ ከነዚህም ጉዳት ከደረሰባቸው አካባቢዎች ለመጥቀስ ያህል በወላይታ ዞን ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ፣ በሰሜን ጎንደር ዞን በጠለምት፣ ጃናሞራ፣ አዲአርቃይ እና የዳ ወረዳዎች፣ በትግራይ ደቡባዊና ምስራቃዊ ዞን ጉሎ መህዳ ወረዳ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ኤፍራታና ግድም ወረዳ፣ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን ደብረሲና ወረዳ እና በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ የደረሰው የመሬት መንሸራተት እና በሥልጤ ዞን ምስራቅ ስልጤና እና ስልጤ ወረዳ፣ በምዕራብ አርሲ ዞን ዶዶላ ወረዳ፣ በጋምቤላ ክልል በጎግ፣ በላሬ፣ ጆርና እና ዋንተዋ ወረዳዎች፣ በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ በነበረው ከባድና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ በሰብሎች፣ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ ካርታ 4)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በነሀሴ ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች እና ግድቦች ላይ ከፍተኛ የእርጥበት ወይም የውሃ መጠን አግኝተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞግቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ እና የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በተለይም በላይኛውና በመካከለኛው በአባይ፣ በተከዜ፣ በኦሞግቤ እና በስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች እጅግ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ነበራቸው፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ በተፋሰሶች በሚገኙ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ የውሃ መያዣዎች እንዲሁም የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ አቅምን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ከነበረው ከባድ ዝናብ እና ተደጋጋሚ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በታችኛቹ እና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ በተወሰነ ሁኔታ ጫና ፈጥሮ ተስተውሏል፡፡ ከነዚህም ለመጥቀስ ያህል በተከዜ፣ በአባይ በአዋሽ፣ በቦሮ አኮቦና ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮ እንደነበር የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

ሴፕቴምበር የክረምት ወቅት የመጨረሻው ወር ሲሆን የክረምቱ ዝናብ ከበርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድበት ጊዜ ነው። በአንፃሩ ደግሞ ቀደም ሲል በክረምት ወራት ብዙውን ጊዜ የተስፋፋ ዝናብ ያልነበራቸው የሀገሪቱ ደቡባዊ ክፍሎች ዝናብ ማግኘት የሚጀምሩበት ጊዜ ነው። በመደበኛው ሁኔታ የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች የፀሐይ አቅጣጫን ተከትለው ከሴፕቴምበር የመጀመሪያው ሳምንት በኋላ ከሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ አካባቢዎች የሚዳከሙ ቢሆንም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በወሩ መጨረሻ ሳምንት ደግሞ ዝናብ ሰጪ ክስተቶቹ እየተዳከሙ በመምጣት ከአብዛኛዎቹ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች በበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ ተፅዕኖ ስር መሆን ይጀምራሉ። የክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች በዚሁ መልኩ በመቀጠል በወሩ መጨረሻ ላይ ዝናብ በሀገሪቱ ሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ደቡብ አካባቢዎች ላይ ይወሰናል፡፡በዚህም መሰረት በመጪው ሴፕቴምበር <u>በምዕራብ አማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ በጋምቤላ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በኦሮሚያ ምዕራባዊ አጋማሽ ላይ የክረምቱ ዝናብ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል ሲሆን፤ በመጠን ረገድ ደግሞ አብዛኛው ትግራይ፤ የአማራ ምሥራቃዊ</u>



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አጋማሽ፤ በመካከለኛው ኦሮሚያ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት አካባቢዎችን ጨምሮ ከመደበኛው በላይና መደበኛ ዝናብ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ በረዶ የቀላቀለና ነጎድጓድ አዘል ከባድ ዝናብ በተለይ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም የምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ማለትም የድሬዳዋ፣ የሐረሪ፣ የሶማሌ ማዕከላዊ ክፍል፣ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ እንዲሁም የአፋር ደቡባዊው ክፍል ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ መጠኑም ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እንደሚሆን ይጠበቃል። በሌላ በኩል ደግሞ የክረምት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች አልፎ አልፎ ወደ ደቡብ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ ከደቡብ ኦሮሚያ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች አልፎ አልፎ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ የደቡብ ሶማሌ አካባቢም በወሩ መጨረሻ ላይ አነስተኛ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1-31/2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፐቴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የሴፕቴምበር ወር የሚኖረው የዕርጥበት ሁኔታ በተለይም ዘግይተዉ ለተዘሩና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙትም ሆነ ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውኃ አቅርቦት እንዲሁም የሚጠበቀው ቀጣይነት ያለው የእርጥበታማ ሁኔታ በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውሰጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል እና በመጠኑ አነስተኛ ቢሆንም ወደ ደቡብ እንደሚሰፋፉ የሚጠበቀው እርጥበት ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ሆነው በሰነበቱትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የጎላ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በሌላም በኩል ከክረምት ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃር ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ተዳምሮ ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ሰለሚችል የሚመለከተው አካል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ በመከታተል አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ በመጠቀምና ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሴፐቴምበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚጥለው ሴፕቴምበር በአባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ የአፋር ደናክል እና የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ደግሞ መጠነኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ የሚኖረው እርጥበትም የውሃ ሀብት ግብዓትን ከማጎልበትም በተጨማሪ በቀሪዎቹ ቀናት ውሃን መያዝ ለሚፈልጉ ግድቦች ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአሁን ወቅት ከፍተኛ ውሃ የያዙ ግድቦች በቀጣይ ከሚያገኙት ተጨማሪ እርጥበት ጋር ተዳምሮ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በግድቡ እና በታችኛው የተፋሰስ ክፍል ላይ ጫና ሊያሳድር ይችላል፡፡ ይህንን ተፅዕኖ ለመቀነስ በተንዳሆ፣በከሰም፣በርብ እና በተከዜ ግድቦች ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et